# በክርስቶስ የነበረው አስተሳሰብ

“በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን፤” — ፊልጵስዩስ 2፥5 (አዲሱ መ.ት)

ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ደብዳቤው ካንፀባረቀው ነገር አንዱ በክርስቶስ የነበረው አስተሳሰብ ነው። በክርስቶስ በነበረው አስተሳሰብ ሕይወታችን እንዲቀረጽ ያዛል። በክርስትና ትምህርት ክርስቶስ ቤዛችንም አርአያችንም ሆኖ ቀርቧል። በቤዛነቱ የዳንን ሁላችንም እርሱን ምሳሌ ወይም አርአያ ማድረግ ይጠበቅብናል።

በክርስቶስ የነበረው ያ አሳብ ወይም አስተሳሰብ ምንድን ነው? ለሌሎች መኖር ወይም ሌሎችን ለመጥቀም ራስን መክፈል ነው። ቀጣዩ ክፍል ይህን ያስረዳል፡-

“እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውንም እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ።” _ ፊልጵስዩስ 2፥4 (አዲሱ መ.ት)

ኢየሱስ አባቱን እግዚአብሔርን ለማክበር እና እኛን ለመጥቀም ምን አደረገ? ሰማይን ትቶ መጣ፣ አባቱን አጉልቶ ተመላለሰ፣ ለእኛ ሲል ራሱን ባዶ አደረገ፣ ይህ ብቻ አይደለም ስለእኛ ሞተ። ቀጣዩ ክፍል ይህን ያብራራል፡-

“እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀው እንደማይገባ አድርጎ አልቈጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፣ በሰውም አምሳል ተገኝቶ፣ ራሱን ባዶ አደረገ፤ ሰው ሆኖ ተገልጦም፣ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።” (ፊልጵስዩስ 2፥6_8 (አዲሱ መ.ት)

የዚህን ያህል ዋጋ እንዲከፍል ያደረገው ራሱን የሚረሳ ትሑት ልብ ስለነበረው ነው። አማኞች ራሳችንን ማዕከል ካደረገ አኗኗር መላቀቅ ይገባናል። ለሌሎች መኖርን መለማመድ አለብን። ለዚህ ደግሞ አስቀድሞ አስተሳሰባችን በክርስቶስ ሕይወት እና ትምህርት መቀረፅ አለበት።

ጳውሎስ "ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ"፤ “ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕትና ቊጠሩ" ያለው የከፍታ ኑሮ ሰዋዊ ፍልስፍና ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ አሳብ ወይም አስተሳሰብ ነው።

“በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።” (ፊልጵስዩስ 2፥5)

ደግሞም አሳብ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ ሕይወት ተገልጿል። (ፊልጵስዩስ 2፥6_8)

ስለዚህ ሐዋርያው ኢየሱስ ለእኛ የሞተበትን ምክንያት እና መንገድ ማለትም ቤዛነቱን ከመግለፅ ባሻገር የሞተበትንም ትሑት ልብ ማስተማሪያ አድርጎታል። ይህ ልብ የጢሞቴዎስ እና የአፍሮዲጡ ኑሮ ላይ ሲንፀባረቅ እናያለን።

የጢሞቴዎስ ኑሮ፡-

“ነገር ግን ኑሮአችሁን ሳውቅ እኔ ደግሞ ደስ እንዲለኝ ፈጥኜ ጢሞቴዎስን ልልክላችሁ በጌታ በኢየሱስ ተስፋ አደርጋለሁ። እንደ እርሱ ያለ፥ ስለ ኑሮአችሁ በቅንነት የሚጨነቅ፥ ማንም የለኝምና፤ ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና፥ የክርስቶስ ኢየሱስን አይደለም።” (ፊልጵስዩስ 2፥19_21)

ጢሞቴዎስ ይጨነቅ የነበረው ስለኑሮው ሳይሆን ስለ ሌሎች ኑሮ ነው። ይፈልግ የነበረው የራሱን ሳይሆን የክርስቶስን ነው።

የእኛን ቅጥ ያጣ ራስ ተኮር አኗኗር የሚገስጽ ሕይወት ነው። ክርስቶስን ከተማርነው እንደዚህ አይነት አኗኗር የሕይወት ዘይቤያችን መሆኑ አይቀርም!. ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ አስተምህሮ ምሳሌነት የሚኖረው ኑሮ እንዲኖረን ያደርጋል!.

የአፍሮዲጡ ኑሮ፡-

“ነገር ግን ወንድሜንና ከእኔ ጋር አብሮ ሠራተኛ ወታደርም የሚሆነውን፥ የእናንተ ግን መልእክተኛ የሆነውና የሚያስፈልገኝን የሚያገለግለውን አፍሮዲጡን እንድልክላችሁ

በግድ አስባለሁ፤ ሁላችሁን ይናፍቃልና፥ እንደ ታመመም ስለ ሰማችሁ ይተክዛል።” (ፊልጵስዩስ 2፥25_26)

አፍሮዲጡ ከጳውሎስ ጋር አብሮ ሠራተኛ ነበረ፤ ያ ማለት የፀጋ ተልዕኮ ልዑክ ነበረ። ጳውሎስን በሚያስፈልገው አገልግሎት ይደግፈው ነበረ። አማኞች መታመሙን ስለሰሙ ተከዘ፤ ለምን? በእርሱ ምክንያት እንዳይጨነቁበት። ጉዳቱን ዋጥ አድርጎ የሚሠራ የክርስቶስ ወታደር ነበረ።

በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አሳብ ወይም አስተሳሰብ (Attitude) ይህ ነው፤ ለሌሎች ምቾት መፍጠር፣ ደብዝዞ ማድመቅ፣ ተጎድቶ መጥቀም፣ ....!. ይህ አኗኗር ከራስ ወዳድነት ነፃ መሆንን ይጠይቃል!.

እንዲህም መኖር በእግዚአብሔር ፀጋ ይቻላል!.

ሐዋርያው “በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።” (ፊልጵስዩስ 2፥5) ብሎ ላነሳው ትልቅ አጀንዳ የክርስቶስን ሕይወት ምሳሌ አድርጎ አቅርቧል። በተጨማሪም ከእርሱ ጋር አብረው ሠራተኞች የሆኑትን የጌታ ባሪያዎች የኑሮ ፍሬ ጠቅሷል። ይህ የሚያሳየው ኑሮው እንደሚቻል ነው!.

ሐዋርያው ስለ አሳብ ወይም አስተሳሰብ መናገሩን ቀጥሏል!. አራተኛው ምዕራፍ ላይ "እነዚህን አስቡ" በማለት ምክሩን አቅርቧል!.

“በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ፤” (ፊልጵስዩስ 4፥8)

ኑሯችን የአስተሳሰባችን ውጤት ነው!. ምንድነው የምናስበው? አእምሯችንን የተቆጣጠረው ምን አይነት አሳብ ነው? ልባችን ምን ፀንሷል? አስተሳሰባችን እኛን ወይስ ሌሎችን ማዕከል ያደረገ ነው?

ሐዋርያው ከላይ የዘረዘራቸውን ነገሮች እንደገና እንመልከት!?

"እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ"

"ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ"

"ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ"

"ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ"

"ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ"

"መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ"

"በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን"

... "እነዚህን አስቡ" እነዚህን ካላሰብን የእነዚህን ተቃራኒዎች አለማሰብ አንችልም!.

ሳይንስ በቀናችን ውስጥ ከ60 ሺህ በላይ አሳቦች አእምሯችንን አቋርጠው እንደሚያልፉ ይናገራል። የትኛውን አሳብ እናሰላስለዋለን? የቱ አሳብ አብሮን ይውላል? ያድራል? ይህን መወሰን የምንችለው እኛ ነን፤ መርጠን ማሰብ እንችላለን!.

ለዚህ ደግሞ አስቀድሞ አእምሯችን ላይ መሥራት ይኖርብናል!. አእምሯችን እንደ ጓሯችን ነው፤ ጓሯችንን አትክልት ከተከልንበት ይጠቅመናል፤ ይህን ካላደረግን አረም እንዳያበቅል ማድረግ አንችልም። አእምሯችን የጸጋውን ቃል ካልዘራንበት ሌላ ማብቀሉ አይቀርም!.

ስለዚህ ዳዊት “አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።” (መዝሙር 119፥11) እንዳለ ከላይ የተዘረዘሩትን ለማሰብ መገኛቸው የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል በልባችን እንሰውረው!.

በርናባስ ዘመነ

2015 ዓ.ም